የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፶፱
አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፬ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

21st Year No 59
ADDIS ABABA 31st July, 2015

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፬/፪ሺ፯ ዓ.ም

ለሻምቡ-ባኮ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ከአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት የተገኘው ብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ....................................................ገጽ ፰ሺ፪፻፹፪

CONTENTS

Proclamation No. 914/2015

Arab Bank for Economic Development in Africa Loan Agreement for Financing the Shambo - Bako Road Project Ratification Proclamation ………..Page 8282

## አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፬/፪ሺ፯

## በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ

ለሻምቡ-ባኮ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል መጠኑ ፲፫ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር (አስራ ሦስት ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር) የሆነ ገንዘብ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት መካከል እ.አ.አ ሜይ ፬ ቀን ፪ሺ፲፭ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፴ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## Proclamation No 914/2015

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE ARAB BANK FOR ECONOMIC DEVELOPMENT IN AFRICA

Whereas, a Loan Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Arab Bank for Economic Development in Africa stipulating that the Arab Bank for Economic Development in Africa provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan amount of Thirteen Million United States Dollars (USD 13,000,000) for Financing the Shambu-Bako Road Project, was signed In Addis Ababa on the 4th day of May 2015;

Whereas, the House of people's Represeatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Loan Agreement at its session held on the 7th day of July,2015;

Now, Therefore, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Constitution, it is hereby proclaimed as follows.

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ ለሻምቡ-ባኮ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት የተገኘው ብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፬/፪ሺ፯ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪. የስምምነቱ መፅደቅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት መካከል እ.አ.አ ሜይ ፬ ቀን ፪ሺ፲፭ በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

**፫. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፲፫ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር (አስራ ሦስት ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሰረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

**፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፬ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as ''Arab Bank for Economic Development in Africa Loan Agreement for Financing the Shambo - Bako Road Project Ratification Proclamation No 914/2015''.

**2. Ratification of the Agreement**

The Loan Agreement signed in Addis Ababa between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Arab Bank for Economic Development in Africa on the 4th day of may, 2015 is ratified.

**3. Power of the Ministry of Finance and Economic Development**

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of Thirteen million United States Dollars (USD 13,000,000) in accordance with the terms and conditions set-forth in the Loan Agreement.

**4. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazzette.

**Done at Addis Ababa on this 31st day of July,2015**

**MULATU TESHOME (DR)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**